Montgomery Hospice & Prince George's Hospice



# እኛ ምን እንደምንሠራ እና እኛ እንዴት እንደምንረዳ

## ሆስፒስ ምንድን ነው?

ሆስፒስ ህይወታቸውን በሚወስን ሕመም ለተያዙ ሰዎች የህክምና እና የግል ምቾት በመስጠት ላይ ትኩረት የሚሰጥ እንክብካቤ ነው። የሆስፒስ እንክብካቤ እንደ ሕመም እና የማቅለሽለሽ ስሜት የመሳሰሉ አካላዊ ምልክቶች ያለባቸውን ሰዎች ይረዳል። የሆስፒስ ሠራተኞች፣ ሕመምተኞች፣ ቤተሰቦች እና ጓደኞቻቸው ስሜታዊ እና መንፈሳዊ ሰላም እንዲያገኙ በመርዳት ያጽናናሉ። በሕመም እና በመለየት ለተጠቁ በሽተኞች ክብር እና ደህንነት ለመስጠት ከሕመምተኞች እና ቤተሰቦች ጋር አብረው ይሠራሉ።

## ሞንትጎመሪ ሆስፒስ እና የፕሪንስ ጆርጅ ሆስፒስ ምንድን ነው?

ሞንትጎመሪ ሆስፒስ እና የፕሪንስ ጆርጅ ሆስፒስ ሜሪላንድ ውስጥ ለ 40 ዓመታት የሆስፒስ እንክብካቤ ሲሰጥ የቆየ ለትርፍ የማይሠራ ድርጅት ነው። ከሆስፒስ አገልግሎቶች በተጨማሪ፣ የሞንትጎመሪ ወይም የፕሪንስ ጆርጅስ ካውንቲዎች ውስጥ ለሚኖር ወይም ለሚሰራ ማንኛውም ሰው ሙያዊ የሀዘን ድጋፍ እንሰጣለን። 2019 ውስጥ፣ ከ 2,300 በላይ ለሆኑ ሕመምተኞች እና ቤተሰቦቻቸው እንክብካቤ ሰጥተናል፣ እንዲሁም ከ 7,500 በላይ ለሆኑ የማህበረሰቡ ነዋሪዎች የሀዘን ትምህርትና ድጋፍ ሰጥቷል።

## ሞንትጎመሪ ሆስፒስ እና የፕሪንስ ጆርጅ ሆስፒስ ማን ነው?

ቀሳፊ በሽታ ጋር የሚኖሩ ጎረቤቶቻችንን ፍላጎቶች ለማሳካት በቡድን አንድ ላይ የምንሠራ ባለሙያዎች እና በጎ ፈቃደኞች ነን። ባለሙያዎቹ፣ ዶክተሮችን፣ ነርሶችን፣ ተለማማጅ ነርሶችን፣ መንፈሳዊ አማካሪዎችን፣ ማህበራዊ ሠራተኞችን፣ ፈቃድ ያላቸው የነርስ ረዳቶችን እና የሀዘን አማካሪዎችን ያካትታሉ።

## ሞንትጎመሪ ሆስፒስ እና የፕሪንስ ጆርጅ ሆስፒስ የማንኛውም ካውንቲ መንግስት ክፍል ነው?

አይደለም።

## ሞንትጎመሪ ሆስፒስ እና የፕሪንስ ጆርጅ ሆስፒስ ከኃይማኖት ቡድን ጋር የተጣመረ ነው?

አይደለም።

## ሞንትጎመሪ ሆስፒስ እና የፕሪንስ ጆርጅ ሆስፒስ የሚንከባከበው ማንን ነው?

(ከሐኪሞቻቸው ጋር ከተነጋገሩ በኋላ) በሽታውን በኃይል ከመጋፈጥ ይልቅ ህይወታቸውን በተሟላ ሁኔታ መኖር ላይ ለማተኮር የወሰኑ ሞንትጎመሪ ካውንቲ እና የፕሪንስ ጆርጅ ካውንቲ ውስጥ ላሉ በጠና ለታመሙ ጎረቤቶቻችን እንክብካቤ እናቀርባለን።

## ሆስፒስ ካንሰር ላለባቸው ሰዎች ብቻ ነው?

አይደለም። ሆስፒስ ማንኛውም በሽታ (ካንሰር፣የመርሳት በሽታ፣ የልብ በሽታ፣ እና ሌሎችን ጨምሮ) ያለባቸውን ሕመምተኞች መርዳት ይችላል።

## ሕመምተኞች ለሆስፒስ ይከፍላሉ?

አይከፍሉም። የሆስፒስ አገልግሎቶች የሚከፈሉት በሚከተሉት ነው፡

- ሜዲኬር
- ሜዲክኤይድ
- አብዛኞቹ የግል መድህን ኩባንያዎች፣ ወይም በ
- ሞንትጎመሪ ሆስፒስ እና የፕሪንስ ጆርጅ ሆስፒስ። መድህን የሌላቸውን ወይም ሌላ መክፈያ መንገድ የሌላቸውን ሕመምተኞች እንንከባከባለን።

## ሕመምተኞች ለምን ሆስፒስን ይመርጣሉ?

ሕመምተኞች ከሕመማቸው መፈወስ እንደማይችሉ ግልፅ ሲሆን፣ እና እስከ ዕድሜያቸው ፍፃሜ የተቻለውን ያህል በምቾት መኖር ሲፈልጉ፣ ሆስፒስን ይመርጣሉ። ለአንዳንድ ሕመምተኞች፣ ሆስፒስ በሆስፒታል ከመቆየት – ወይም ወደ ሆስፒታል ከመመለስ – መልካም አማራጭ መሆን ይችላል።

## ሕመምተኞች የሆስፒስ እንክብካቤ የሚያገኙት የት ነው?

ለሕመምተኞች እና ቤተሰቦቻቸው በሚኖሩበት ቤት ውስጥ፣ የትም ቢሆኑ እንክብካቤ ይሰጣል። ከቤቶች እና ከአፓርትመንቶች በተጨማሪ፣ በአዛውንቶች መኖሪያ እና በነርሲንግ ቤቶች እንዲሁም በኬሲ ሀውስ (Casey House)፣ ለሆስፒስ ሕመምተኞች ብቻ የተሰራ የጤና እንክብካቤ ተቋም፣ ውስጥ እንክብካቤ ይሰጣል።

## በሞንትጎመሪ ሆስፒስ እና የፕሪንስ ጆርጅ ሆስፒስ ምን አገልግሎቶች ይሰጣሉ?

- ሙያዊ የሕመም እና የምልክቶች ማስታገሻ
- መድሃኒቶች
- የህክምና መሣሪያ፣ እንደ ኦክስጅን፣ ተሽከርካሪ ወንበሮች፣ መራመጃዎች፣ እና የሆስፒታል አልጋዎች
- የህክምና ቁሳቁሶች
- በቀን 24 ሰዓታት በሳምንት 7 ቀናት በአካል የሚገኙ ነርሶች
- ምን እንደሚጠብቁ እና እንዴት እንደሚቋቋሙት ላይ ትምህርት
- ለሕመምተኛ የግል እንክብካቤ እገዛ
- ማሟያ ሕክምናዎች
- በጎ ፈቃደኞች
- የሀዘን ድጋፍ

## ለሕመምተኛው እንክብካቤ የሚሰጠው ማን ነው?

ሕመምተኛውን ለመንከባከብ በሕብረት የሚሠሩ የባለሙያዎች ባለተሞክሮ ቡድን – ሀኪሞች፣ ነርሶች፣ የሆስፒስ ረዳቶች፣ ማህበራዊ ሠራተኞች፣ መንፈሳዊ አማካሪዎች፣ እና የሰለጠኑ በጎ ፈቃደኞች።

## የሆስፒስ ሀኪም ሕመምተኛውን ይጎበኛል?

አዎ። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ የሆስፒስ ሀኪም የሕመምተኛውን ቤት ይጎበኛል።

## የሆስፒስ ነርሶች ምን ይሠራሉ?
የሆስፒስ ነርሶች ሕመምተኞችን በየጊዜው በመጎብኘት እንዴት እንደሆኑ ያያሉ፣ እንክብካቤ ሰጪዎች ለሚወዷቸው እንክብካቤ እንዴት እንደሚሰጡ ያስተምራሉ እና ሌሎች የሆስፒስ ቡድን አባላት ጉብኝቶችን ያስተባብራሉ።

## ፈቃድ ያለው የነርስ ረዳት ምንድን ነው?
ፈቃድ ያለው የነርስ ረዳት (CNA) የግዛቱን ማረጋገጫ ፈተና ያለፈ የሰለጠነ የነርስ ረዳት ነው። የእኛ CNAዎች ሕመምተኞችን በየጊዜው እየጎበኙ ሰውነታቸውን በማጠብ እና በደህና እንዲንቀሳቀሱ በማረጋገጥ ይረዳሉ።

## የሆስፒስ ማህበራዊ ሠራተኛ ሥራው ምንድን ነው?
የሆስፒስ ማህበራዊ ሠራተኞች ሕመምተኞችን እና ቤተሰቦቻቸውን ቤታቸው ውስጥ እንዴት ምቾት እንደሚያገኙ እና እንደሚቋቋሙ ያሰለጥኗቸዋል። በተጨማሪም፣ ሕመምተኞች እና ቤተሰቦች በጥልቅ ውይይቶች ወይም በተግባራዊ ሥራ እንደ የዘወትር ሥራዎች በማቀናጀት መርዳት ይችላሉ።

## የመንፈሳዊ አማካሪ ሥራ ምንድነው?
ለሚፈልጉ ሕመምተኞች፣ ስለ መንፈሳዊ ጉዳይ ስጋቶች ለማነጋገር መንፈሳዊ አማካሪዎች አሉ። መንፈሳዊ አማካሪዎቻችን ሰዎች እንደየእምነታቸው ለጥያቄዎቻቸው እና ምቾታቸው መልስ እንዲያገኙ የሚረዱ ናቸው። የመንፈሳዊ አማካሪዎች የማንኛውም ኃይማኖት ተከታይ የሆኑትን፣ ያልሆኑትንም ጨምሮ፣ መንፈሳዊ ድጋፍ ይሰጣሉ እንዲሁም ሰዎች የራሳቸውን መልስ እንዲያገኙ ይረዳሉ።

## የበጎ ፈቃደኞች ሥራ ምንድን ነው?
ከሶስት ቀናት ጥልቅ ስልጠና በኋላ፣ በጎ ፈቃደኞች በተለያዩ መንገዶች፣ እንክብካቤ ሰጪዎች ዕረፍት እንዲያገኙ ሕመምተኞችን በመጎብኘት፣ እጆቻቸውን ለማፍታታት በማሸት፣ በመላላክ ወይም ሕመምተኞችን እና ቤተሰቦችን ኢ-ሜይል፣ ደብዳቤ ወይም ማስታወሻዎችን መጻፍ ላይ በማገዝ ይረዳሉ። በጎ ፈቃደኞች በዓመቱ ውስጥ በሚሰጠው ተከታታይ ስልጠና ላይ መሳተፍ አለባቸው።

## ለሕመምተኞች እንክብካቤ ውሳኔዎች የሚወሰኑት እንዴት ነው?
ሞንትጎመሪ ሆስፒስ እና የፕሪንስ ጆርጅ ሆስፒስ የሕመምተኞቻችንን ፍላጎት ያከብራል። የእነርሱ ምርጫ በቃዳሚነት ይመራናል።

## ሕመምተኛው ሆስፒስ ሲመርጥ የቤተሰቡ ሀኪሞች ተሳትፎ ይኖራቸዋል?
አዎን፣ ሕመምተኞች የሆስፒስ እንክብካቤ በሚያገኙበት ጊዜ ሀኪሞቻቸውንም መጠቀም ይችላሉ። ሀኪሞቻቸው ግቦች እና የእንክብካቤ እርምጃዎችን ለመገምገም ከሆስፒስ ሀኪሙ ጋር ይማከራሉ።

## የሆስፒስ ሕመምተኞች ሁሉንም መድሃኒቶች ማቆም አለባቸው?
የለባቸውም።

## የሆስፒስ ሕመምተኛ አደጋ ቢደርስበት ምን ይከሰታል - ተጨማሪ እንክብካቤ ይቀርብለታል?
አዎ።

## ሆስፒስ ሞትን ያፋጥናል?
አያፋጥንም። በአንዳንድ ሁኔታዎች ሆስፒስ ሕመምተኞች ለረጅም ጊዜ እንዲኖሩ ይረዳል።

## ሕመምተኞች ወይም ቤተሰቦች የሆስፒስ እንክብካቤን ከፈለጉ ወይም ስለሆስፒስ ጥያቄዎች ካሏቸው ምን ማድረግ አለባቸው?
- የሆስፒስ እንክብካቤን ሊያካትቱ የሚችሉትን ሁሉንም ያላቸውን አማራጮች እንዲነግራቸው ሀኪማቸውን መጠየቅ
- ለመረጃ መደወል ወይም መረጃ ለመስጠት እንድንጎበኛቸው መጠየቅ
- ከተጨማሪ ጥያቄዎች ጋር መደወል። ሞንትጎመሪ ሆስፒስ እና የፕሪንስ ጆርጅ ሆስፒስ ቤተሰቦች አማራጮቻቸውን በደንብ እንዲረዱ ይፈልጋል፣ እንዲሁም ማንኛውንም ውሳኔ ያከብራል።



## ለሆስፒስ እንክብካቤ የተመዘገቡ ሕመምተኞች ሀሳባቸውን መቀየር ይችላሉ?
አዎ። ሕመምተኞች የሆስፒስ እንክብካቤን በማንኛውም ምክንያት በፈለጉ ጊዜ ማቆም ይችላሉ። በማንኛውም ጊዜ ደውለው የሆስፒስ አገልግሎቶችን በድጋሚ መጀመር ይችላሉ።

## ሕመምተኞች የሆስፒስ እንክብካቤን በዘላቂ ያቆማሉ?
አዎ። አንዳንድ ሕመምተኞች ተሽሏቸው ከሆስፒስ ይወጣሉ።

## ኬሲ ሀውስ (Casey House) ምንድን ነው?
ኬሲ ሀውስ ለሆስፒስ ሕመምተኞች የተዘጋጀ ሞቃት ቤት መሰል ህንጻ ነው። አንድ ሕመምተኛ ልዩ ትኩረት የሚፈልጉ ምልክቶች ካሉት፣ ሕመምተኛው ለአጭር ጊዜ ወደ ኬሲ ሀውስ መሄድ ሊኖርበት ይችላል - ምልክቶቹ ቁጥጥር ስር ከዋሉ በኋላ፣ ሕመምተኛው ወደ ቤት መመለስ ይችላል።
ኬሲ ሀውስ ሀኪሞች፣ ነርሶች፣ የተመሰከረላቸው የነርስ ረዳቶች፣ ማህበራዊ ሠራተኞች፣ መንፈሳዊ አማካሪዎች እና በጎ ፈቃደኞች አሉት።

## ኬሲ ሀውስ ከሌሎቹ ድርጅቶች በምን ይለያል?
ኬሲ ሀውስ ለመጨረሻው የህይወት ዘመን እንክብካቤ ለመስጠት በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠኑ ሙያተኛ ቡድኖች አሉት። ሕመምተኞች የግል መኝታ ቤቶች ከግል መታጠቢያ ክፍሎች ጋር አሏቸው። አዋቂዎች፣ ልጆች እና እንስሳ ጎብኚዎች በቀን 24 ሰዓት መጎብኘት ይችላሉ።

## ሀዘን ምንድን ነው? እዝን ምንድነው?
## ሞንትጎመሪ ሆስፒስ እና የፕሪንስ ጆርጅ ሆስፒስ እንዴት ይረዳል?
ሀዘን አንድ የሚወዱት ሰው ሲሞት በጥልቀት የሚሰማ የማዘን ስሜት ነው። ”እዝን” የሚለው ቃልም፤ ያንን የመከፋት ጊዜ የሚወክል ተመሳሳይ ስሜት ነው። የሚወዱት ሰው ለሞተባቸው በኋላ ለ 13 ወራት ቤተሰቦችን የሚደግፉ ከፍተኛ የባለሙያ ዲግሪ ያላቸው አማካሪዎች አሉን።
ይህ ድጋፍ ለቤተሰቡ ያለምንም ወጪ በስልክ ማማከር፤ ቡድኖች፣ ወርክሾፕች፣ እና በፖስታ መላክን ያካትታል።

## ሞንትጎመሪ ሆስፒስ እና የፕሪንስ ጆርጅ ሆስፒስ ሀዘን የደረሰበትን ሕብረተሰብ እንዴት ይረዳል?
በስራ ቦታ ውስጥ ለማህበረሰብ ቡድኖች እና ሠራተኞች የሀዘን ትምህርት እናቀርባለን። አጋዥ ቡድኖች እና ወርክሾፖች ሞንትጎመሪ ወይም ፕሪንስ ጆርጅ ካውንቲዎች ውስጥ ለሚኖር ወይም ለሚሰራ ማኛኛውም ሰው ነጻ ናቸው።